# <u>መዋሸት ታሪክን አያጠፋም</u>

ወያኔ ኢሕአፓን ይጠላዋል--ይህ ትኩስ ዜና አይደለም። ኢትዮጵያን የሚጠሉ ሁሉ ኢሕአፓን ይጠላሉ--ይህም የታወቀ ነው። ወንጀለኞች፣ የደርግ ሽብርተኞችና ነፍሰ ገዳዮች ም ሁሉ ኢሕአፓን አምርረው ይጠላሉ--ይህም የሚጠበቅ ነው። ኢሕአፓ ባይኖር ኖሮ ሕዝብን ማወናበድና ማታለል እንችል ነበር የሚሉ ሕዝብን የሚንቁም አሉ። የክህደት ልፈፋቸው በሕዝብ ሲወገዝ፣ ቅሌታቸው ሲጋለጥ፣ አወቅን መጠቅን ብለው ሊዘባነኑ ሲነሱ ቀፎነታቸው ሲጋለጥ ለውደቅተቀቸው ሁሉ ኢሕአፓን የሚከሱና የሚወነጅሉ አሉ። በተለይ በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ውጠረት የገባው ወያኔ በኢሕአፓ ላይ ዘመቻውን አጧጡፏል። ስብሐ ት ነጋ ሳይቀር ኢሕአፓ ላይ እየዘላበደ ነው። የወያኔ ቅጥረኞችና ሰርጎ ገቦችም በየድረገፁ ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻቸውን አጠናክረዋል። የነገይቷን ኢትዮጵያ ዕጣ ሊቃኙ የተነሱትም ባዕዳን ይህን ሴራ ኢሕአፓ ያጋልጥብናል ብለው በቅድሚያ ዘመቻ ከፍተውበታል። ሀገርና ሕዝብን በሻዕቢያ ዕቅድ መሰረት ለገንጣዮች አሳልፈው ሊሰጡ የተቀጠሩና የተሰማሩ ወራዶችም ሕዝብ አንቅሮ ሲተፋቸውና ሲያወግዛቸው በንዴት ኢሕአፓን ማውገዙን ተያይዘ ውታል። ጠላት ሲያጠቃህ ኩራ ነውና ኢሕአፓ በዚህ ሁሉ ቅስሙ አልተሰበረም። በወያኔ ቅጥረኝነት መፅሀፍና ታሪክ ፃፍን ብለው በሚውገረገሩም አተላዎች ላይ ይስቃል እንጂ ሚዛ ን የሚሰጥ አልሆነም ።

በቅርቡ የደርግ አባል የነበረው ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ የተባለው ግለሰብ ደግሞ በሚገ ርም ሁኔታ ለአንድ በውጭ ሀገር ያለ የአንድ ድርጅት ቴሌቪዥን ጣቢያ በሰጠው ቃለ መጠ ይቅ በመንግሰቱ ኃይለማርያም ላይ ተሞክሮ የነበረውና ለብዙ ጄኔራሎች ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነውን የያኔ ግንቦት መፈንቅለ መንግስትን በተመለከተ በሴራው ሻዕቢያንም ወያኔንም ኢሕአፓንም አማክረን ነበር ሲል ተናግሯል። ይህ ኢሕአፓን በተመለከተ የደርጉ ሻለቃ የተናገረው ፍፁም ሀሰት ከመሆኑ ሌላ በአሁኑ ጊዜ ይህን ሀሰት ማሰራጨቱ ለምንስ አስፈለገ የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑ አልቀረም። ኢሕአፓ ሀገራችንን በሚመለከት የተካሄዱትን ሴራዎች፣ በባዕዳን የተጠነሰሱ ተንኮሎችን ወዘተ ጠንቅቆ የሚያውቅና በቂ መረጃ ያለው ቢሆንም እነዚህኑና ለሴራዎቹ ተባባሪ የሆኑትን ግለሰቦችን ከማጋለጥ የተቆጠበ ው ከወቅቱ የትግል ትኩረቱ አንፃር አይጠቅምምም ከሚል እንጂ መረጃዎቹን በመድረክ ሊያቀርብ ቢነሳ ብዙዎች እንኳን መድረክ ሊወጡና ሊለፍፉ ቀርቶ ከሚደበቅቡት ጉድጓድ ባልወጡ ነበር። ሻለቃ ዳዊት ለምን ሀሰት መናገር እንደመረጠ ወይም እንደተገደደ የምናው ቀው የለም ግና ስለዚያን ጊዜ ፀረ ደርግ መፈንቅለ መንግስት ካነሳ ዘንዳ ዕዳ በራሱ ብለን የሚከተለውን ማብራሪያ መስጠት እንገዳዳለን።

ለብዙ ጄኔራሎች ዕልቂት ምክንያት የሆነው የዚያን ጊዜ መፈንቅለ መንግስቱ ሴራ የተዘጋጀው በአሜሪካው መንግሰት ሲአይኤ ተብሎ በሚጠራው የስለላ ደርጅት ነበር:: ሻለቃ ዳዊትም በዚሁ ተቋም ተመልምሎ ወይም ተባብሮ ለመስራቱ መካድ የሚችለው ጉዳይ አይደለም:: እነ ሻለቃ ዳዊት በአሜሪካ አቀነባባሪነትና በሻዕቢያ ተባባሪነት መንግስቱን እንጥላለን ብለው በየዋህነት አሰቡ ብንልም እንኳን የሻዕቢያና አሜሪካ ዓላማ ግን የተለየ መሆኑ ግልፅ ነበር:: አሜሪካና ሻዕቢያ ዓላማቸው የደርግን ጦር መከፋፈልና ማዳከም ሲሆን እነ ሻለቃ ደግሞ ሻዕቢያም ተኩስ አቁም ያደርጋል፤ በኢትዮጵያዊነትም ይሰለፋል በሚል አምነው ነበር:: ዛሬ አነግ ኢትዮጵያዊነትን ተቀበለ እንደሚሉን ጅሎች ማለት ነው:: ይህን ሴራ ለማገዝ በአሜሪካ ግፊት ሱዳንም ተሰማርታ ነበር:: ሻለቃ ዳዊትም ሱዳን መጣ፤ ወደ ኤርትራም ዘለቀ :: ማንንም ኢሕአፓን አላገኘም:: ከሻዕቢያም ፤ከወያኔም ከነታምራት ላይኔ ም በሜዳ ተገናኘ :: ይህ ሁሉ ለሻለቃውም ለአሜሪካም ምስጢር መሆኑ ነበር፤፤ ግና እንኳን ኢሕአፓም ደርግም ያወቀው ጉዳይ ነበር:: ሻለቃ ዳዊት ማንንም የኢሕአፓ ሰው በዚህ ጊዜ አላገኘም--አሌ ካለ መደረኩ ክፍት ነውና አሌ ይበል እስቲ:: ለግንቦት የታሰበው መፈንቅለ መንግስት በየካቲትና መጋቢት ተጋልጦ የነበረ ነው:: ለመንግስቱ ኃይለማርያም ምስራቅ ጀርመንና ዩጋንዳ ማስጠንቀቂያ ሰጥውት ነበር:: እስራዔልና እንግሊዝ ስለ መፈንቅሉ መረ ጃ ለማሰባሰብ በመጋቢት ሲወራጩና ግራ ቀኙን ሲጠይቁ ነበር:: ኢሕአፓም የሻለቃውን ወደ ኤርትራ ማለፍና ከዚያም ስላደረገው ውይይት መረጃ ስለነበረው ከግንቦት በፊት ባወጣ ው ዜና መፅሄት ዕትሙ በርዕሰ አንቀፅ ደረጃ በደፈናው የመፈንቅለ መንግስት አማራጭ መፍትሄ አለመሆኑን በመተቸት ለሴረኞቹም ጥቆማ ሰጥቶ ነበር:: በዚህ ላይ ብዙ ማለት ቢቻልም ለጊዜው በዚሁ እንለፈው:: ለመንግሰቱ ኃይለማርያም ሠየቅርብ አጋሮች ለተስፋዬ ወልዴ ስላሴና ለመንግሰቱ ገመቹ ይፃፉ የነበሩ ደብዳቤዎች ምሳሌ ናቸው:: በመፈንቅለ መን ግዝት ደረጃ ም ቢሆን ዝርክርክና ሙያተኛነት የጎዳለው አንጉል ሙከራ መሆኑ ግልፅ ነበር፡ የጦሩን መሪዎች አስጨርሰውና ሰራዊቱን ሞራል አሳጥተው ለሻዕቢያ ሰለባ ሊያደርጉ ላቀ ዱት ግን እነ ሻለቃ ዳዊት አዋቂም ሆኑ አላዋቂ ሆነው አገልግለዋል ማለት ይቻላል:: ሻዕቢያ ን አሰቸግረውት የነበሩ ጄኔራሎች ተገደሉና ለሻዕቢያ አመቺ ሁኔታ ተፈጠረለት:: ዛሬ ሻለቃ ዳዊት ሀሰት መጠረቅ ሳይሆን ለባዕድመሳሪያ ሆኜ ነበር ብሎ ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ በተገባውና ባማረበትም ነበር::

ኢሕአፓ ከሻለቃ ዳዊትም ሆነ ከማንም ጋር መፈንቅለ መንግሰት ሴራ ውስጥ አልገባም፡ በአሜሪካ የስለላ ደርጅትና በሻዕቢያ በተጠነሰሰ ሴራ ውስጥ ኢሕአፓ ትላንት ቀርቶ ዛሬም የሚገባም አይደለም:: ማን ቢወልድ ማ! ሻለቃ ዳዊት የራሱን ግግደ መስቀል ራሱ ይሸከም እንጂ ወደ ኢሕአፓ ጫንቃ ለማሳለፍ ባይሞክር ጥሩ ነው:: ኢሕአፓ ሻዕቢያ ተኩሰ አቁም

አድርጎ የ 30 ዓመት የመገንጠል አባዜውን ይተዋል ብሎ አላመነም:: ይህን መሰል ቅዠት ፖለቲካው ዝብርቅርቅ ላለባቸው ሻለቆችና ቀፎ ዶክተሮች የሚተው እንጂ ኢሕአፓን የሚ መለከት አይደለም:: ኢሕአፓ ነብርን ድመት እኮ ነው ሲል የሚሰማ አልነበረም/አይደለምም :: ዛሬ በኢሕአፓ ላይ ልዩ ልዩ ክፍሎች አፀያፊ ዘመቻ አጧጡፈዋል:: ምክንያታቸው ብዙ ነው:: የደርግ ርዝራዥ ወንጀለኞች የታሪክን ፍርድ ይፈራሉና ይፋረዳናል የሚሉትን ኢሕአ ፓም ማጥፋትይፈልጋሉ--የሚፋረዳቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ማመን አይፈልጉምና ነው:: የደርግ ሽጉጥ ታጣቂ ሰማያዊ ዩኒፎርም ለባሽ ካድሬና የፍልስፍና ፕሮፌሰር ዛሬ ታጋይ ተብሎ ያን ትውልድ እያወገዘ ከወያኔ ጋር ዕርቅን እየሰበከ መድረከ ይዟል:: የኢሕአ ፓ ወጣተ ታጋይ የሆነውን በሳንጃ ዓይኑን ሊያጠፋ የጫረውም ባንዳ ዛሬ አዋቂ ፕሮፌሰር አ ኮኖሚስት ተብሎ በየስብሰባው ይጋበዛል:: እነዚህና መሰልና የባሱ ነፍሰ ገዳዮች ባባዕድ ሀገር ተወሽቀውና ወንጀላቸውን ሸፋፍነው ቢገኙም ኢሕአፓ ያውቀናል ይፈረዳናል ባይ ናቸውና በድርጅቱ ላይ ሳያሰልሱ ይዘምታሉ:: ኢሕአፓ የወቅቱ የሀገርና የዜጎች ሁሉ ጠላት የመለስ አገዛዝ ነው ብሎ ቢሰለፍም ቢታገልም እነዚህ ሁሉ ያፈሰሱት ደም ያቃዣቸዋልና ትኩረታቸ ው በኢሕአፓ ላይ ሆኖ አሳፋሪ ውሸቶችን ሲለፍፉ ይደመጣሉ:: የሻለቃ ዳዊት የሀሰት ንግግ ርም በዚህ መልክ የሚታይ መሆኑ አልቀረም::

ኢሕአፓ ዚያድ ባሬና የሶማሊያን ወረራ ደገፈ ፤ ኢሕአፓ ባይኖር ኖሮ ኤርትራኖችም አይገ ነጠሉም ነበር፤ ኢሕአፓ ከአረቦችና ሲ አይ ኤ ጋር ገጥሞ አሴረ፤ ጠርሙሰ ፈጭቶ ሚሊሺያ ውን አብልቶ ጨረሰ፤ ካቶሊክ ነበርና ለቫቲካን አገለገለ፤ ኢትዮጵያ ትገንጠል ብሎ ታገለ፤ ወዘተ ወዘተ --ያልተሰራጨ አሳፋሪ ሀሰት የለም:: ዋናው ጥያቄ ለምን የሚለው ነው? አሰራ ጮቹስ እነማን ናቸው? ለምን ይዋሻሉ? ለምን ራሳቸውን በሀሰት ልፈፋ ያዋርዳሉ? መልሱ ከላይ እንዳስቀመጥነው ግልፅ ነው:: ሻለቃ ዳዊት የስብሐት ነጋ የውሸት ዘመቻ አጃቢ መሆኑ ለራሱሊያሳስበው ይገባል--ሰልፉ በእውን ከሕዝብ ጋር ከሆነ :: ጡት የሚጣባው ከባዕዳን የ ወያኔ አለቆች ጋር ከሆነ ግን ስምሪቱ በትዕዛዝ ነውና ተልዕኮውን እናውቅበታለን ማለት ነው :: ሻለቃውም ሆነ መሰሎቹ ግን ማወቅ ያለባቸው አንድ ሀቅ ኢሕአፓ ጥቃቱና ዘመቻው ሲያ ይልበት ይበልጥ አምርሮና ተጠናክሮ ለሕዝብና ለሀገር እንደሚታገል ነው:: ኢሕአፓ የተመ ሰረተው በ1964 ዓመተ ምህረት ነው--እስከዛሬም ለማንም ባንዳ ፤ አምባገነን፤ ባዕድ እጅ አ ልሰጠም:: ለዋሾዎች፤ ቀፎ ዶክተር በሉን ባዮች ወይም የባዕድ ቅጥረኞችም አልተንበረከከም:: ዛሬ 40 ዓመት ሊሞላው ሲል ያውም ለኢምንቶች ውሸትና ውዳቂ ዘመቻ ሊቸነፍ እንዴት ይጠበቃል?

ሻለቃውም በጠራራ ፀሀይ ዋሽቷል:: ዋሽ ያሉትም እንዲሁ በገሀድ ተጋልጠዋል:: በመዋሸት ታሪክ አይሰረዝም አይለወጥም:: ይህን መገንዘቡ ይጠቅማል::